የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 3
ADDIS ABABA - 23rd October, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ለአነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፮፻፵፫

## CONTENTS

Proclamation No. 91/1997
International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Financing the Small Scale Irrigation Project Ratification Proclamation ........................ Page 643

**አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም (ኤስ.ሲ.ፒ II) ማስፈጸሚያ የሚውል ፳፪ ሚሊዮን ፮፻ ሺህ (ሃያ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ በሮም የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለአነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO.91/1997

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 22,600,000 USD (twenty two million six hundred thousand United States Dollars) for financing the Small Scale Irrigation Programme (SCP II), was signed in Rome, on the 16th day of July, 1997;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 23rd day of October, 1997;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles(1) and (12) of the constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Financing the Small Scale Irrigation Project Ratification Proclamation No. 91/1997."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ጁላይ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ በሮም የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በስምምነቱ የተገኘውን ፳፪ ሚሊዮን ፮፻ ሺህ (ሃያ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed in Rome on the 16th day of July, 1997 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 22,600,000 USD (twenty two million six hundred thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 23rd day of October, 1997.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of October, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING INTERPRISE